# የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

ሚያዝያ ፡ 16 ፡ ቀን ፥ 1983 ፡ ዓ.ም. ።

# የኢ.ህ.ሥ.አ. ፡ የዕርቅ ፡ ሐሳብ ፡ ማስተካከያ ፡ ነጥቦች ።

*[በሚያዝያ ፡ ወር ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ በተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ ኹነቶች ፡ ("ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ") ፡ መንግሥት ፡ ሸምጋይነት ፥ እብሪታንያ ፡ መዲና ፡ ለንደን ፡ ለተቀጠረው ፡ ሀገራዊ ፡ የዕርቅ ፡ ጉባኤ ፥ ኢ.ህ.ሥ.አ. ፡ አቅርቦት ፡ የነበረው ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሐሳብ ። ]*

የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ሰራዊትና ፡ የተቃራኒዎቹ ፡ ነጻ ፡ አውጪ ፡ ድርጅቶች ፡ ውጊያ ፥ ለኢትዮጵያ ፥ ወጣቶቿን ፡ ከማሳጣትና ፡ የተረፉትንም ፡ አካለ ፡ ስንኩል ፡ ከማድረግ ፥ አዝመራዋን ፣ ሥራዋን ፣ ንግዷን ፡ በኹለት ፡ ፊት ፡ ከመከልከል ፥ ረኃቧን ፡ ከማጽናትና ፡ ጠቅላላ ፡ ሀገራዊ ፡ ችሎቷን ፡ ከማድከም ፡ በቀር ፡ የሚያበረታ ፡ አይኾንም ።

የሪፓብሊኩ ፡ (ኢ.ሕ.ዴ.ሪ.) [1] ፡ እና ፡ የተቃራኒዎቹ ፡ ንባበ ፡ ኀሊ. [2] ፥ ሥር ፡ መሠረታቸው ፡ በእውነት ፡ የጸኑትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ እምነቶች ፥ ባሕርያዊ ፡ የኾነ ፡ ሥልጡንሕዝብናዋን ፡ የሚፃረርባት ፡ እስከ ፡ ኾነ ፡ ድረስ ፥ ላታምንላቸውና ፡ ላትከተላቸው ፥ አንዳቸው ፡ አንዳቸውን ፡ ለመሻር ፡ መዋጋታቸው ፡ ከንቱ ፡ ነው ። በተለይም ፥ ዛሬ ፥ የዐመፁ ፡ ተጠሪ ፡ ሊ. ፡ ኮሎኔል ፡ መንግሥቱ ፡ ኀይለ ፡ ማርያም ፥ የውጊያውን ፡ ሜዳ ፡ ጥሎ ፡ ከኼደና ፥ በይዘቱ ፡ የተተኩት ፡ ኀላፊዎች ፡ ተኵስ ፡ እንዲቆም ፡ ከለፈፉ ፡ ወዲያ ፡ መዋጋቱ ፥ ለክርክራቸው ፡ መፍጃ ፡ ሥልጡንሕዝብናን ፡ ["ዴሞክራሲ"ን] ፡ ከተቀበሉ ፡ ወዲያ ፥ በሰላም ፡ ንግግር ፡ እያለ ፥ በጦር ፡ ግድድል ፡ መቀጠሉ ፥ ካኹን ፡ በፊት ፡ ከተዋለው ፡ ኹሉ ፡ የከፋውን ፡ በደል ፡ በሀገር ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ ይኾናል ።

ተኵስ ፡ ማቆሙና ፡ በሰላም ፡ ዕርቅ ፡ መደራደሩ ፡ ግን ፥ ለኢትዮጵያ ፥ ያፈ ፡ ሙዝ ፡ ሥልጣንን ፡ የሚያርቅላት ፡ ዕድል ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ ስለሚያምን ፥ ኢ.ህ.ሥ.አ. ፡ ሐሳቡን ፡ ተቀብሎታል ። እመልካም ፡ ፍጻሜም ፡ እንዲደርስ ፡ ከልብ ፡ በመመኘት ፥ መምህር ፡ መስፍን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ በረገዱ ፡ ላቀረቡት ፡ የሰላም ፡ ዕርቅ ፡ ውጥን ፥ የበኩሉን ፡ መስተካከያ ፡ ሐሳብ ፡ እንሆ ፥ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ያቀርባል ።

**፩ ፤ የተኵስ ፡ ማቆም ፡ መሠረቶች ።**

፩.፩ ፤ ኹለቱ ፡ ወገን ፡ ተደራዳሪዎች ፡ ማንኛውንም ፡ ክርክራቸውን ፡ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ ሊያደርጉ ፡ እንዲዋደዱ ።

፩.፪ ፤ ያገሩን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ክዋኔ [3] ፡ መሥራት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያንድነቱ ፡ የተቀደሰ ፡ ባሕርያዊ ፣ ትውፊታዊና ፡ ሕጋዊ ፡ መብት ፡ መኾኑን ፡ ኹለቱም ፡ ወገን ፡ ተነጋጋሪዎች ፡ እንዲተማመኑ ።

፩.፫ ፤ ይህን ፡ ጉልማዊ ፡ ተገባሩን ፡ እንዲያከናውንለት ፥ ሕዝቡ ፥ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ አግባብ ፥ መርጦ ፡

---

1 ኢ.ሕ.ዴ.ሪ. ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝባዊ ፡ ዴሞክራስያዊ ፡ ሪፓብሊክ ።

2 ንባበ ፡ ኀሊ. ፤ ኀሊ.ኛ ፡ (ideology) ።

3 ክዋኔ ፤ ሕገ ፡ መንግሥት ።

የሚሠይማቸው ፡ ወኪሎቹ ፥ ባልተጨቈነ ፡ ኅሊና ፥ ባልተጨነቀ ፡ ልቦና ፥ በጉባኤ ፡ መክረው ፣ ዘክረው ፥ የምታስማማቸውን ፡ ርትዕ ፡ ባልተገደደ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ለማጽናት ፡ የሚያሻቸውን ፡ ሰላም ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፥ ኹለቱም ፡ ወገን ፡ ተዋጊዎች ፡ በየግንባራቸው ፡ ተኵስን ፡ እንዲያቆሙለት ።

፩.፬ ፤ ክዋኔውን ፡ አጠናቀው ፡ ባዋጅ ፡ አጸኑ ፡ ድረስ ፥ አገሪቱን ፡ ያስተዳድርለት ፡ ዘንድ ፥ ሕዝቡ ፥ በእግዚእናው ፡ መርጦ ፡ እሚሠይመው ፡ ጊዜያዊ ፡ ርእሰ ፡ ሀገር ፡ ትእዛዝ ፡ ሥር ፡ ኾኖ ፡ በመሥራት ፥ የሀገሪቱን ፡ የውስጥና ፡ የድንበር ፡ መከላከልን ፡ ተግባር ፡ እንዲያከናውኑ ።

፩.፭ ፤ መደምደሚያውን ፥ ጉባኤው ፥ በታሰበለት ፡ ሰላምና ፡ ምቾት ፡ ሠርቶ ፥ በነጻነት ፡ ያወጀውን ፡ ክዋኔ ፡ ሕጋዊ ፡ አድርገው ፡ ሊቀበሉ ፡ ቃል ፡ እንዲገቡ ።

## ፪ ፤ የሰላም ፡ አመሠራረት ።

መምህር ፡ መስፍን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፥ በቅን ፡ መንፈስ ፡ እንዳሳሰቡት ፦

፪.፩ ፤ ከእየክፍለ ፡ ሀገሩ ፥ ከእየእምነቱ ፡ ኅብረት ፥ በቀና ፡ ሰውነታቸው ፥ በጠቅላላ ፡ ዕውቀታቸውና ፡ በሸንጎ ፡ ተሰሚነታቸው ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ከኾኑት ፡ ዐዛውንት ፡ መኻከል ፥ ከመቶ ፡ የማይበዙ ፥ የዕርቅ ፡ ሸማግሌዎች ፡ ተመርጠው ፥ በምክራቸውና ፡ በቍጥጥራቸው ፦

፪.፩.አ ፤ በትውፊታዊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የግዛት ፡ ሥርዐት ፥ ኢትዮጵያዊ ፡ ውልድና ፡ በአገሬነት ፡ በሕግ ፡ የታወቀ ፡ መጤ ፡ እኩል ፡ የምርጫ ፡ መብት ፡ የነበራቸው ፡ ሲኾኑ ፥ ዛሬ ፥ የኢ.ሕ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፥ ጠቅላላውን ፡ ሕዝብ ፡ በመደብ ፡ ለያይቶ ፥ የሚበዛውን ፡ ወገን ፡ ኢትዮጵያዊ ፥ ዜግነቱን ፣ ርስቱን ፣ ንብረቱን ፣ ሥራውን ፡ አለሕግ ፡ አሳጥቶ ፥ የመምረጥ ፡ መብቱን ፡ ነሥቶት ፡ ስለሚገኝ ፥ ኢትዮጵያዊ ፡ ኹሉ ፥ የጾታ ፣ የእምነት ፣ የማኅበራዊ ፡ ደረጃ ፣ የሥራ ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግበት ፥ እኩል ፡ የምርጫ ፡ መብት ፡ ይኖረው ፡ ዘንድ ፥ የተነሡት ፡ መብቶቹ ፡ ኹሉ ፡ እንዲመለሱለት ።

፪.፩.በ ፤ የይዞቱን ፡ ውንብድና ፡ በመሸሽ ፥ ከኢትዮጵያ ፡ ውጭ ፡ ተሰደው ፡ የሚኖሩ ፥ የመራጭነት ፡ መብታቸውን ፡ በሕግ ፡ ያልተነፈጉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ኹሉ ፥ እምርጫ ፡ ወረዳው ፡ ገብተው ፡ ለመምረጥና ፡ በሥርዐቱ ፡ ለመመረጥ ፡ ሙሉ ፡ መብት ፡ እንዲኖራቸው ።

፪.፪ ፤ የምርጫው ፡ መብት ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ከተስተካከለ ፡ በኋላ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ከ 200 ፡ ሺሕ ፡ እስከ ፡ 300 ፡ ሺሕ ፡ ነዋሪዎች ፡ ላለው ፡ የምርጫ ፡ ወረዳ ፡ ወይም ፡ **"ሠሪጌ"** [4] ፥ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ ሥርዐት ፡ ኹለት ፡ ሰዎችን ፡ መርጦ ፡ በመወከል ፥ ያገሩን ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ ኹነት ፡ የሚሠራለትን ፡ አንድ ፡ ሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ ያቆማል ።

፪.፫ ፤ የዕርቅ ፡ ሸማግሌዎች ፡ ችሎት ።

፪.፫.አ ፤ በመራጮች ፡ ዝኀባ ፣ በምርጫው ፡ አከናወን ፡ ውጤት ፡ የሚነሣውን ፡ ውዝግብ ፡ ዳኝነት ፡ ያያል ። ብይኑም ፡ ይግባኝ ፡ አይባልበትም ።

፪.፫.በ ፤ የምርጫውን ፡ ውጤት ፡ መርምሮ ፡ ያጸድቃል ። ውሳኔውም ፡ የመጨረሻ ፡ ነው ።

፪.፬ ፤ ከዋኙ ፡ ጉባኤ ፥ የክዋኔውን ፡ ሥራ ፡ አጠናቆ ፡ እጨረሰ ፥ ከዚያም ፥ በሕዝባዊ ፡ ፈረዳ [5] ፡ አጽድቆ ፥ በሕግነቱ ፡ ዐዲስ ፡ ርእሰ ፡ ሀገር ፡ እስከተሾመና ፡ መንግሥት ፡ እቆመ ፡ ድረስ ፥ እውስጥም ፡ እውጭም ፡ ካሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መኻከል ፡ መርጦ ፡ ይሠይማል ። ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፥ ሊቀ ፡ መንበሩን ፡ በተርታ ፡ ድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ይሾማል ።

## ፫ ፤ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ።

፫.፩ ፤ ጊዜያዊ ፡ ርእሰ ፡ ሀገር ፥ ለተመረጠለት ፡ ሀገራዊ ፡ የዐናት ፡ ተግባር ፥ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በመታመን ፡ የሚሠቀ ፡ መኾኑን ፡ በወግ ፡ ያስታምናል ።

፫.፪ ፤ ጊዜያዊ ፡ ርእሰ ፡ ሀገር ፥ ለኹለቱም ፡

---

4 <u>ሠሪጌ</u> ፤ ምኳንያ ፥ የሀገሪቱን ፡ ክዋኔ ፡ (ሥርዐት) ፡ ከሚከውኑት ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር ፡ አንዱ ፡ ከዋኝ ፡ ወይም ፡ ሠሪ ፡ ምድር ፥ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የምርጫ ፡ ወረዳ ፡ (constituency) ።

5 <u>ሕዝባዊ ፡ ፈረዳ</u> ፤ ውሳኔ ፡ ሕዝብ ፡ (popular referendum) ።

ወገኖች ፡ እኩል ፡ የራቀ ፥ ለተግባሩ ፡ የተገባ ፡ ሰው ፥ ከኢትዮጵያ ፡ ታማኝ ፡ አገልጋዮች ፡ መኻከል ፡ መርጦ ፡ ለጊዜያዊው ፡ መንግሥት ፡ መሪን ፡ ይሾማል ።

፫.፫ ፤ ለሚኒስትሮቹ ፥ የመንግሥቱ ፡ መሪ ፡ ወይም ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፥ ከኹሉም ፡ ወገኖች ፥ ለሥራው ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውንና ፡ ለዐደራው ፡ የሚበቁትን ፡ ታማኞች ፡ ይመርጣል ።

፫.፬ ፤ ለጠቅላይ ፡ ጦር ፡ መምሪያው ፡ ሹም ፥ ከኹለቱም ፡ ወገን ፡ የጦር ፡ ሰራዊቶች ፡ ጠብ ፡ ያልተቃባ ፥ ለሥራው ፡ የተገባ ፥ ባገር ፡ ፍቅሩ ፡ የማይዛባ ፡ አዝማች ፡ መኰንንን ፡ መርጦ ፡ ይሾማል ።

፫.፭ ፤ ለጦር ፡ አዛገሮቹ ፥ ከኹለቱም ፡ ወገን ፡ ሰራዊቶች ፥ ተግባብተው ፡ ሊሠሩ ፥ ተማምነው ፡ ሊሰማሩ ፡ ይችላሉ ፡ የሚላቸውን ፡ መርጦ ፡ ይሾማል ።

፫.፮ ፤ በሕግ ፡ መሠረት ፡ መርጦ ፡ የሚሾመውን ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትርና ፡ በእግዚአና ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ የሚያውላቸውን ፡ ሚኒስትሮች ፣ የጦር ፡ አለቃዎችና ፡ ዳኞዎች ፡ ለከዋኙ ፡ ጉባኤ ፡ አቅርቦ ፡ ያሳምናል ።

፫.፯ ፤ ከዋኙ ፡ ጉባኤ ፥ ጊዜያዊው ፡ መንግሥት ፡ ሥራውን ፡ ጨርሶ ፡ የሚለቅበትንና ፡ ዘላቂው ፡ መንግሥት ፡ ለዘለቄታው ፡ ተግባር ፡ የሚተካበትን ፡ ወግና ፡ ሥርዐት ፣ ቀንና ፡ ሰዓት ፡ በሕግ ፡ ይወስናል ።

፫.፰ ፤ ጊዜያዊው ፡ መንግሥት ፥ ዘላቂው ፡ መንግሥት ፡ በሥራው ፡ ሊተካው ፡ በተወሰነለት ፡ ቀንና ፡ ሰዓት ፥ ሥራውን ፡ በወግ ፡ ለቅቆ ፥ ሥፍራውን ፡ አስረክቦ ፡ ይሰናበታል ።

በተረፈ ፥ መምህር ፡ መስፍን ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ «*ፌዴራሊዝም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ትውፊታዊ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ሊታወስ ፡ ይገባል*» ፡ ሲሉ ፡ በጨረፍታ ፡ የጠቀሱት ፥ የነበረ ፡ የሚመስል ፥ ያልነበረ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህውም ፥ ማንኛውም ፡ ሀገራዊ ፡ (ዜጋ) ፡ ወይም ፡ የሀገራውያን ፡ ኅብረት ፡ (የዜጎች ፡ ኅብረት) ፡ ግዴታውን ፡ በሚችለውና ፡ በሚመቸው ፡ ኹኔታ ፡ በመፈጸም ፥ ራሱን ፡ ካንድነቱ ፥ ማለት ፡ ከመንግሥቱ ፡ ጋራ ፡ የበለጠ ፡ ለማዋሐድና ፡ ለመጥቀም ፡ እንዲመቸው ፡ የተሰጠ ፡ መብት ፡ እንጂ ፥ እንዲያርቀውና ፡ የባሰ ፡ እንዲበድለው ፡ የተሠራ ፡ ሥርዐት ፡ አይደለም ።

መዠመሪያ ፡ ነገር ፥ ኢትዮጵያ ፥ ካንዲት ፡ ብሔር [6] ፣ ካንድ ፡ ሕዝብ ፣ ባንድያ ፡ ሥልጣን ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በመኖር ፡ ጨርሳ ፡ የተዋሐደች ፡ ሀገር ፡ ናት ፡ እንጂ ፥ ወደ ፡ መዋሐድ ፡ እንደሚኼዱ ፡ ሀገሮች ፥ እንደተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ ኹነቶች ፡ ("ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ") ፣ እንደ ፡ ሶቪዬት ፡ ኅብረት ፤ ወይም ፡ ለመዋሐድ ፡ እንደሚፈልገው ፡ እንደ ፡ አውሮፓ ፡ ኅብረትም ፡ አይደለች ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፥ አዋሐጆቿ ፡ ክፍሎች ፡ እንደተራራቁ ፡ ተለያይተው ፡ እንዲጠበቁ ፡ እንደምታደርገው ፡ እንደ ፡ ስዊስም ፡ አይደለች ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ በታሪኩ ፡ እንደታየው ፥ በሀገራዊ ፡ ችሎቱ ፡ መክሮ ፣ ዘክሮ ፥ ሕጉን ፡ ላንድነቱ ፡ በዐዋጅ ፡ ያናግራል ። በሕግነቱ ፡ ተቀብሎ ፥ ባፈጻጸሙ ፡ ብቻ ፥ እንዳገሩ ፡ ያየር ፡ ጠባይ ፣ የሰብል ፡ ዐይነት ፣ የመሰብሰቢያ ፡ ወቅትም ፡ ይለያል ። ሕዝቡም ፥ እኩል ፡ ጌትነቱን ፣ እኩል ፡ ሀገራዊነቱን ፡ (ዜግነቱን) ፡ እንጂ ፡ የመብት ፡ መዛነፍን ፡ አይወድም ። ፌዴራሊዝምን ፡ ቢጭኑትም ፡ አይቀበል ። የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፥ ባ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ. ፡ ም. ፥ በኤርትራ ፡ ቢጭኑባት ፥ ባ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ፡ ም. ፡ አውልቃ ፡ ወርውራዋለች ። ነገር ፡ ግን ፥ መምህር ፡ መስፍን ፡ እንዳሉት ፡ ኹሉ ፥ ጕዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ለነገሩ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ የኾነውን ፥ ሕዝቡን ፥ አንድነቱን ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ለርሱው ፡ ልንተውለት ፡ ይገባል ፨

*ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ (ሊ. ፡ ዤኔራል) ፥*

*የጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፥ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ።*

---

6 ብሔር ፤ ምድር ፡ (territory) ።